# ዘገባ ከሰማይ ቤት

### ክፍል-ሁለት

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

በምድር ሳለሁ አንዳንድ ብርጭቆ፣ ብርሌ ወይም መለኪያ መጨበጥ የሚያዘወትሩ ሰዎች እንደ አሳ መጠጢቱን ሳብ-ጅው፤ ብድግ-ግጥም ያደርጉና ህሊናቸው ላይ የተጠመጠመው ማሰሪያ ተተርትሮ ሲወድቅ "ነፍሴን አስደሰትኳት!" ሲሉ እሰማ ነበር። ብዙዎች እንደዚሁ "ነፍሴን አላሰቃያትም!" በሚል ስጋን የመውደድ ፈሊጥ የሌሎችን ነፍስ ከሚያሰቃዩት ጋር እያበሩ ወይም አላይም አልሰማም ብለው አውቀው እየተደበቁ ለአፈር ቀለብ የሚሆነውን ስጋቸውን እንደ እንቁላል ሲንከባከቡ አስተውል ነበር። መቼም "በልጅ አመካኝቶ ይበላሉ አንጉቶ" ሆኖ ነው እንጅ የሚደሰትማ በአልኮል የነሆለለ ነፍስ ሳይሆን ልቅ-አካል፣ ወይም ቅይዱን የፈታ ስጋ ነው። አዎ እውነቱን እንጨዋወት ከተባለ ግፍ ከሚፈጽሙት ጋር መዋልማ የኋላ ኋላ እንኳን ለነፍስ ለስስታሙ ስጋ እንኳን አይበጅም።

ምናልባት የረሳችሁኝ ካላችሁ ይህንን ወግ የማወጋችሁ ነፍስ ነኝ። ስጋ የለበሰ ሰው ነፍስን መርሳቱ መቼም እንግዳ ነገር አይደለም። አበው እንኳን አገጫቸውን በመዳፋቸው አስደግፈው በትዝብት "ወይ ስጋ ለባሴ" ሲሉ ስጋ ውስጥ ተደብቄ እሰማቸው ነበር። ነፍስን የዘነጋ ስጋ የለበሰች ነፍስ ደግሞ በሌላዋ ነፍስ ላይ ሞትን፣ ግርፋትን፣ እስራትን፣ ስደትንና ሌሎች-ሌሎችንም ግፍኞች እንደምትፈጽም "እህ…" እያላችሁ ብታዳምጧት የራሳችሁ ነፍስ አንድ በአንድ ትነግራችኋላች። እስቲ ለአንድ አፍታ በበሽታ፣ በርሃብ፣ በስደት፣ በእስራትና በባሩድ ምክንያት ከስጋ የተለዩትን እንደዚሁም በመሰቃየት ላይ ያሉትን ነፍሶች እንድታስታውስ ለነፍሳችሁ አጋጣሚውን ፍጠሩላት። በተመሳሳይ መንገድም በሽታን፣ ርሃብንና ስደት በሚዘሩ፤ ባሩድ እየተኮሱ ነፍስን ከስጋ በሚለዩ፣ እንደዚሁም ከድሃ ጉረሮ እየሞለቀቁ ከሚደልቡ ከንቱ ገላዎች ውስጥ የሚኖሩ ነፍሶችንም እንድታጤን እድሉን ስጧት። እርግጥ ነው የያዛችኋትን ነፍስ እንደ አበሻ ልጅ መሐል አናቷ ላይ በኩርኩም እያቀለጣችሁ "ዝም ብለሽ ኑሪ!" ካላላችኋት በስተቀር አሁን እኔ እንደማወጋችሁን ወግ ሁሉ ተኝታችሁም ሆነ እየሄዳችሁ አንድ ባንድ ትነግራችኋለች። እውነቴን ነው! እስቲ ለሆዳችሁ የምትቸሩትን አንድ መቶኛ ጊዜ እንኳን ለነፍሳችሁ ስጡና በጥሞና የምታጫውታችሁን ቅመሱብኝማ! ነፍስን ከማዳመጥ ይልቅ ከርሴን እየሞላሁ ድንጋይ መፍለጥ ወይም ክብርን ሸጦ ከጋማ እንሰሳ ጀርባ ላይ እንደሚጫን ቆርበት ወይም ኬሻ ሲያገለግሉ መኖር ይቀላል የሚል አካል እንደማይጠፋ እኔ ስጋ ለባሸዋ ነፍስ እረዳለሁ፤ አይቻለሁም።

ከላይ በተገለጠው መንገድ ነፍስን የለበሰ ገላ አፈር እስከሚበላው ድረስ በሚያሳየው የተወሳሰበ ባህሪ የተነሳ ሰዎች ነፍስን በተለያዬ መልክ ይመለከቷታል። ነፍስን ለምን በአንድ፣ በሁለትና በሶስት ምልክ እንደሚያይዋት በክፍል-አንድ* ዘገባ ውስጥ በመጠኑ ተገልጿል። ነፍስ ከሶስትም በላይ ናት ብለው የሚከራከሩ ተመራማሪዎች ነፍስን ሸፍኖ የያዛት የሰው አካል ለአቅመ-አዳም ወይም ለአቅመ-ሔዋን ከደረሰ በኋላ በውስጡ ካለችው ነፍስ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት መሰረት በማድረግ ነው። እንደምታውቁት ህሊና በልጓሙ ሸብቦ ካልገታው በስተቀር፤ የሰው ስጋ ስግብግብ፣ ቅብጥብጥ፣ አመለኛ፣ ስስታም፣ ጨካኝ፣ ግፈኛ፣ ውሸታም፣ ከዳተኛ፣ ወስላታ፣ ቀልብ- የለሽ፣ ወሮ-በላ፣ ወንበዴ፣ ይሉኝታ-ቢስ ወዘተርፈ ነው። አዎ ህሊና ያልገታው ስጋ ከወባ፣ ሳንባ ነቀርሳ፣ ተስቦና ኤድስም በባሰ ሁኔታ  ሕዝብን የሚፈጅ ጀርም ነው።

ታዲያ እኔ ነፍስ እንደሚገባኝ ነፍስ ከሶስት አይነትም በላይ ናት የሚለው መሰረተ-ሐሳብ የተገነባው ስጋና ህሊና የስልጣን ጦርነት በሚያደርጉበት ሜዳ ላይ በሚሮነኝ ስፍራ ላይ ነው ብዬ አምናለሁ። እንደምታውቁት እነ ብሩክ መንደር ህሊና ስጋን ሞተር ወፍጮ ውስጥ እንደ ገባ ሰርገኛ ጤፍ ድቅቅ አድርጋ አልማው ስተገኝ እነ እኩይ-ፈልስጣ ሰፈር ግን ስጋ ህሊናን ከውስጡ ውልጭ አድርጎ ፍቆ ለአመል እንኳ እንዳይቀር በእንዶድ፣ በአመድና በሞራ ሳሙና ጭምር እሽት አድርጎ አጥቦ አስወግዶት ይገኛል። በዚህም የተነሳ ስጋ ቅይዱን እነደፈታች ያልተገራች በቅሎ አንዴ ዳንኪራ ሲመታ ሌላ ጊዜም ሲራገጥ፣ እንደ ወተት ዝንብም በየቦታው ጥልቅ ሲል ከዚያም አልፎ ምድር እንኳ የማትችለውን ግፍና መከራ በሌሎች ላይ ሲፈጽም ይውላል። ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ይህንን ስንክ-ሳር የሆነ የስጋ ባህሪ የተሸከመችን ነፍስ ብጹዕ-ነፍስ፣ ሚዛን-ነፍስ፣ ደመ-ነፍስ፣ ጅል-ነፍስ፣ አረመኔ-ነፍስና እስስት-ነፍስ ብለው በመሰየም ከሶስትም በላይ መልክ ይሰጧታል።




**ብጹእ ነፍስ** ስጋን ድቅቅ አድርጋ አልማ በቁጥጥሯ ስር ያደረገች የበቃች ነፍስ ናት። ብጹእ ነፍስ ከመላእክት የምትለየው በምድር ላይ ስትኖር ስጋ በመልበሷ ነው። ብጹእ ነፍስ ጊዜዋን የምታሳልፈው ለሹመት ስጥቋምጥና ንብረት ስታግበሰብስ ሳይሆን ሌሎች ነፍሶች የሰመጡበትን መከራና ችግር በጾም፣ በጸሎትና በግብር ለመቅረፍ በመዋተት ነው። አንባቢያን ሆይ! በዚህ ዘመን እንዲህ አይነት ነፍስ የለበሰች ስጋ በአካባቢያችሁ ፈልጋችሁ ማግኘታችሁ አጠራጣሪ ነው። አይደለም እንዴ? እንዲያው ከውስጣችሁ በምትወራጨው ነፍስ ይዣችኋለሁና ብጹእ አቡነ እገሌ፣ ብጹእ ጳጳስ እንትና፣ ብጹእ ሼክ ማንትስ፣ ብጹእ ፓስተር እገሌ እያላቸው ጨዋታዬን አታቋርፍዱብኝ፤ እናንተም ከአንገት በላይ በመናገርና ቃሎችን አላግባብ በመጠቀም ኩነኔ ውስጥ አትግቡ። ለቅዱሳን መላእክትና ሐዋርያት የተሰጡትን ቅድስናና ክብር ገላጭ ማእረጎች ያለ ምንም ይሉኝታ ደረት ላይ ለጥፎ፣ አካልን በተዋበ ካባና በጌጥ በተሽቆጠቆጠ ቆብ ለብጦ ብጹእ ቅዱስ ገብርኤል፣ ሚካኤል፣ ሩፋኤል፣ ጳውሎስ፣ ማርቆስ፣ ማትያስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ ወዘተ  መባል በግፍ ወይም በውስልትና የረከሰ አካል ውስጥ ያለችን ነፍስ ብጹእ እንደማያደርጋት የምታጡት አይመስለኝም። እንዲያውም እንዲህ አይነቱ ስርብትና ነፍስን የበለጠ ቆሻሻና እርኩስ ያደርጋታል። ይልቁንስ ድሃ ለስለት ባስገባው ስለት ወይም አስራት ጮማ እየቆረጡና በሉመዚን እየተንፈላሰሱ ሳይሆን ይህችን አለም ንቀው ሽንብራ እየቆረጠሙ በዱር በገደሉ ከነፍሳቸውና ከአምላከቸው ጋር በግፍ ስለሚገደሉትና ስለሚሰቃዩት ፍጡራን ሲነጋገሩ ውለው የሚያድሩ በምድርም ሆነ በሰማይ ብጹአን ሲባሉ የሚኖሩ ነፍሶች አሉ። እንደ አለመታደል እንዲህ አይነቶች ብጹአን- ነፍሶች በአረመኔ-ነፍሶች እየታደኑ እንደ ሰሜን ዋልያና እንደ ባሌ ቀበሮ እየመነመኑ ሄደዋል። የሚያሳዝነው ታዲያ እነዚህ ቅዱሳን የዋልያና የቀበሮን ያህል እንኳን ከጥፋት የሚያድን ተከራካሪ ቡድን አጥተዋል።

**አረመኔ-ነፍስ** ብዙውን ጊዜ በወንድ ጾታ ይመሰላል። አረመኔ-ነፍስ ብጹእ ነፍስ የምትተገብረውን ተቃራኒ ተግባር ሌተቀን የሚፈጽም፤ አማኞች “ምናምን የለከፈው” ብለው የሚጠሩት ነፍሰ-በላ ነፍስ ነው። አረመኔ- ነፍስን የያዘ ሰው ሳጥናኤል ከምትሉት የሚለየው የሰው ስጋ ስለለበሰ ሲሆን ሰው የሚባለው ደግሞ ተክለ ቁመናው ሰው ስለሚመስል ብቻ ነው። አረመኔ ነፍስን በውስጡ የያዘ አካል የህሊና አልማዙ አንድም ሲፈጠር ያልነበረ አለዚያም ሙሉ በሙሉ ከናላው ላይ በሞረድ ተፍቆ፣ በከሰል፣ በአመድና በእንዶድ ታጥቦ በምትኩ በተንኮልና በክፋት ደለል የተሞላ ነው። በዚህም የተነሳ አረምኔ ነፍስን ሽክፎ የያዘ አካል በውሸት፣ በክህደት፣ በስርቆት፣ በማታለል የተካነ፤ መያዣ መጨበጫ የሌለው፤ ቅቤ እንደተቀባ ሌጣ ገላ ሲያሙለጨልጭ የሚኖር አዳላጭ ፍጡር ነው። አረመኔ- ነፍስ ስሙን ያገኘው የለበሰው ገላ ሌሎችን ነፍሶች ከስጋቸው ሲያለያይ የሚውል ጸረ-ነፍስ ጉድ ስለሆነ ነው። አዎ አረመኔ-ነፍስ የህጻናትን፣ የጎልማሶችና በአዛውንትን ገላ  በርሃብ፣ በበሽታ፣ በእስራት፣ በዛቻ፣ በስደትና በባሩድ እሳት እየቆላ ነፍስን ሲያሰቃይና ከስጋ ሲያለያይ እርካታ ይሰማዋል። አረመኔ-ነፍስን በውስጡ ተሸክሞ የሚንቀሳቀስ ያልተባረከ ገላ ስንቱን ልጅ ያለወላጅ ስንቱን ወላጅም ያለልጅ ያስቀራል። በዚህም ምክንያት የግፉ ቀማሽ የሆኑ ቤተሰቦችና እንዲሁም ሌሎች ጥቁር ለብሰው፤ እንባቸውን እያወረዱና ፊታቸውን እየነጩ፤ በቤታቸውም ሆነ በማምለኪያ ስፍራዎች “አምላክ ሆይ የአረመኔ-ነፍስን ጉዳይ በጥበብህ አሳየኝ!” እያሉ ጡዋትና ማታ በመረረ ሐዘን ይጸልያሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የአረመኔ-ነፍስ ማደሪያ ገላ የራሱን ኮቴ እንኳን የማያምን፣ ኩሽ ባለቁጥር የሚባንን፣ ፈሪ፣ ጠርጣራና ተቅበዝባዥ ፍጡር ነው። በዚም ምክንያት አንዳንድ ሰዎች “አረመኔ-ነፍስን ይዞ የሚሽከረከር ከንቱ ፍጡር ከሞት በፊትም ሆነ በኋላ እየተቅበዘበዘ ኩነኔ ውቂያኖስ ውስጥ ተዘፍቆ የሚኖር የበሰበሰ፣ የነፈረቀና የተላ አካል ነው!” ይላሉ።

**ሚዛን-ነፍስ** ስሟ እንደሚያመለክተው ስጋዋንና ህሊናዋን እያመዛዘነች የምትኖር ነፍስ ናት። ሚዛን ነፍስ እንደ ብጹእ ነፍስ አለምን ንቃ ስጋዋን ረስታ የመኖር ብቃት ባይኖራትም በሌሎች ነፍሶች ላይ ግፍና መከራ ለመፈጸም የተሰራችበት ዝሃ አይፈቅድላትም። ሚዛን- ነፍስን የተጎናጸፈ ገላ ህሊና የማይቀበለውን ነገር አይፈጽምም። ሚዛን ነፍስ ክብሯንና መብቷን ተገፋ እንደ እንሰሳ መኖርን አትቀበልም። ሚዛን ነፍስ በሌሎች ላይ ግፍ እንደ ዝናብ ሲወርድም እንዳላዬ አታልፍም፤ ሆነ ብላም እንደመስቀል ወፍ አትደበቅም። ሚዛን ነፍስ ከሆድ በላይ ህሊና የሚባል አለቃ አላት። ሚዛን ነፍስ የሚጓጓን ሆድ፣ የሚሳሳን አይን፣ የሚቅበዘበዝን መንፈስ ታሰክናለች። ሚዛን ነፍስ ለሰው የሰውነቱ መለኪያ ናት። ሚዛን ነፍስ በምድር ሳለች ክብር አላት። በሰማይ ቤትና በታሪክም ብሩክ ናት።

**ደመ-ነፍስ** ዝም ብሎ እንደ እንሰሳ እየባላ እየጠጣ ኖሮ  በምድር ላይ ምንም ዱካ ሳይተው ጊዜው ሲደርስ በኖ የሚጠፋ ገላ ውስጥ ያለችን ነፍስ ለመግለጽ የሚጠቀሙብት ሐረግ ነው። በክፍል-አንድ እንደተገለጸው ነፍስን በሶስት የሚከፍሉት ጠቢባን ይህ አይነቱን ነፍስ ትንኝ-ነፍስ ይሉታል። አዎ በደመ-ነፍስ የሚንቀሳቀስ ሰው የሚያውቀው ነፍሱ ስጋውን እስከተለየች ድረስ በልቶና ጠጥቶ ከላይ ከላይ እያገሳ መተኛት ብቻ ነው። ደመ-ነፍስን ብቻ የተሸከመ ሰው ቀንበር ከሚሸከም በሬና ጋሪ-ከሚጎትት ፈረስ የሚለየው ሰው ስለሚመስል ነው። ስራማ መጥረቢያም፣ አህያም፣ ባቡርም ይሰራሉ። ፉርሽካ የሚያበሉት ፈረስ ወደ አጋሰስነት የመቀየር ባህሪ እንዳለው ሁሉ ደመ-ነፍሳዊ ሰውም ወደ ሆድ የሚዋጥ ወይም ሌላ አይን ውስጥ የሚገባ ቁሳዊ ጥቅም ካሳዩት ወደ ጅል-ነፍስ ፍጡር የመቀየር ባህሪ አለው።

**ጅል-ነፍስ** ባጭሩ አረመኔ-ነፍስ እንደ መጥረቢያ፣ እንደ ሞፈር፣ ቀንበር፣ እንደ ቁና፣ ወንበር፣ መርቴሎ ወይም እንደ አፍንጫ መጥረጊያ መሐረብ የሚጠቀምበት ገላ ውስጥ የምትገኝ ነፍስ ናት። ጅል ነፍስ ለአላፊ ቁሳዊ ጥቅም ስትል እንደ ደመ-ነፍስ ክብሯን አሳልፋ ከመስጠትም ባሻገር ሌሎች ክብራቸውን ወይም ነፍሳቸውን እንዲያጡ ተግታ በመሳሪያነት ታገለግላለች። እርግጥ ነው ጅል ነፍስ የአረመኔ-ነፍስ ወንጀል መፈጸሚያ ቀኝ እጅ ናት። እንዲያውም ጅል-ነፍስ አንዳዴ ከአረመኔ ነፍስም ትከፋለች። ለምሳሌ አረምኔ ነፍስ “ይታሰር” ብሎ ሲያዝዝ ጅል-ነፍስ ጌታዋን ይበልጥ ለማስደሰት “ይሰቀል እንጅ!” ብላ ታርፈዋለች። አረመኔና ጅል-ነፍስ አብረው ነው የሚኖሩት። አዎ ጅል ነፍስ ባትፈጠር ኖሮ አረመኔ ነፍስ አይኖርም ነበር። እስቲ ለደቂቃ አካባቢያችሁን ቃኙ! ምን አስተዋላችሁ? የጅል-ነፍስ ጎርፍ? የነፍስ ጅልነትም እንደ ጎርፍና ሞኝነት እያሳሳቀ ስለሚወስድ እንዳይጠርጋችሁ ተጠንቀቁ!

**እስስት-ነፍስ** ከብጹእ ነፍስ ጋር ስትገናኝ ብጹእ ለመምሰል፣ አረመኔ፣ ሚዛን፣ ደመ-ነፍስም ሆነ ጅል-ነፍስን ስትገናኝ ደግሞ እነዚህኑ ለመምሰል ልብስ እየቀያየረች ስታጌጥ የምትውል መሰሪ ነፍስ ናት። እስስት-ነፍስ ጅል-ነፍስንና አረመኔ ነፍስን በማገናኘት የደላላ ስራ ትሰራለች። እስስት-ነፍስ ብጹእንና ሚዛን ነፍስን ለማሳሳት በጌጥ ስትመለጥ ትውላለች። እስስት ነፍስ አረመኔ ነፍስንም ለማታለል የሌላትን ልብስ ተበድራ ትለብሳለች። እስስት-ነፍስን ለመለየት ሁለት አይኖች በቂ አይደሉም። አራት አይኖች፣ ሶስት ጆሮዎችና ሁለት አፍንጮች ያስፈልጋሉ። ከእስስት-ነፍስ ይጠብቃችሁ።

*ይህንን ሁሉ ስናወጋ መቼም አእምሯችሁ አበበንና ደበላን ከዚህኛው፣ ሐጎስንና አብደላን ከዚያኛው፣ ዘበርጋንና ጦናን ከአንዱ፣ ስሚዝንና ቭላድሚርን ከሌላኛው ወዘተ ለመመደብ መቃጣቱ አይቀርም። መቼም የሌሎችን እያዩ የራስን ነፍስ መርሳት ውብ አይደለም። እንዲያው እናንተ እያንዳንዳችሁ የተሸከማችኋት ነፍስ የትኛዋ  አይነት ትሆን ይሆን? ህሊናው እንደ ቆላ ፍየል ቆዳ ተገፎ ላልወደቀ ሰው እንዲህ አይነት ጥያቄ ጨጓራን ቁርጥ -ቁርጥ፣ አንጀትን ባርባር፣ ልብን ጭንቅ-ጭንቅ መንፈስን ደግሞ ፍስስ-ፍስስ የሚያደርግ ይመስለኛል። ለማንኛውም ውበት ለማሳመር በነጋ ቁጥር ማበጠሪያ፣ ጺመ መላጫ፣ ጉትቻ፣ ቅባትና ሌሎችንም ጌጣጌጦች ይዛችሁ ከንፈርን ክፍት ክድን፤ ቅንድብን ከፍና ዝቅ እያረጋችሁ በመስተዋት አገላብጣችሁ ከምታዩት ነገ-ፈራሽ ገላ ውስጥ እኔን ዘላለማዊቱን ነፍስም እያያችሁ ምን አይነት ነፍስ እንደሆንኩ ፈትሹኝ፤ መርምሩኝ። ነፍስ ነኝ። ጠዋት ከመስዋቱ ጋ እንገናኝ! ነጋቲ ቡላ!*

*ዘገባ ከሰማይ ቤት ክፍል-አንድ http://addisvoice.com/amh/zegeba.pdf   http://quatero.net/pdf/neffis.pdf

*የካቲት ሁለት ሺህ ሁለት ዓ.ም.*